# ይበሉኝ ቆሞ ቀር

መጥፎውን አውግዤ - ፍቅርን በሰበኩሁኝ
ካለፈው ተምረን-
ደግ ነገር እና'ርግ-
ልዩነት እናጥብብ-
አንድ እንሁን ባልሁኝ:
በስንት ተፈተንሁኝ!

ስንት መከራ ችየ-
ስንት ግፍ አልፎብኝ:
ከጉዳቴ ጋራ-
አልሞትሁም አለሁኝ: :
ቁስሌም አልጠገገ-
አካሌም አልጠና-
መንፈሴም አልረጋ:
ልቤ ግን ሸፈተ-
ሄደ ዱር ከተተ-
እምቢ አለ አሻቀለ-
ነጻነት ፍለጋ: :

የተበላው ሁሉ-
የተጠጣው ሁሉ-
አይነምድር ሆኖ-
ሽንት ሆኖ ሊወጣ:
ላሂያችን ሲሟጠጥ-
ጉልበታችን ሲደክም-
የፋፋው ገላችን-
እንደጉድ ሲተረሽ-
ልዩ አመል ሊያመጣ:
ይቅርብኝ ይህስ ጉድ-
በምኑ ልደሰት-
በማለት አምርሮ:
አይናችን ተግባሩን-
ፍጹም ሲያስተጓጉል-
ሁሉ ነገር ወና-
ሁሉም ሊሆን ዜሮ:
ክፉ መስራት ለምን!
ሀጢያት ምን ሊጠቅም!
ስጋን ከነፍሳችን - ነፍስን ከፈጣሪ

ከማጣላት በቀር፡፡

የስካሁኑ ሳያንስ-
ምኑን ደግ ልሰማ ከእንግዲህ በኋላ-
ለምንስ ሊበጀኝ!
በማለት ጆሯችን-
ስራውን ሲያቋርጥ-
ሁሉም ነገር ድፍን-
ዙሪያው ጸጥ ረጭ ሲል፡
ሁለት ነገር ብቻ የሚነዘንዘን-
የሚጨቀጭቀን-
በሰው ተመስሎ፡
የሰራነው መጥፎ-
ያላረግነው ጥሩ-
ከውስጥ ተሰንቅሮ፡፡

በኔ የመጣውንስ-
እንደየአመጣጡ እቀበለዋለሁ፡
ነገር ግን ሰዎቹ -
ሳይሉኝ ወልጆ-
ባርነትን ላወርስ-
ለምን እፈቅዳለሁ፡
ኋላ ጸጸቱንስ-
እንዴት እችላለሁ!

ቅሬታ ሳይገባኝ - በደስታ መንፈስ
አይኔን ባይኔ ልየው ማለት የምችለው፡
ፍትሀዊ ስርአት ሲሰፍን ብቻ ነው፡፡

እናም ወገኖች-
መላው ኢትዮጵያዊ-
ተነስተን ባንድነት፡
እናስተካክል ሜዳ-
የምንመክርበት፡
ቡቃያወቻችን - የሚቦርቁበት፡
በሰላም በፍቅር - አብረው የሚያድጉበት፡፡

እኔ በበኩሌ-
ልጆ በባርነት - ሲንገላታ ከማይ-
ሳይፈልግ ጎትቸው ወደ ቀውስ ምድር፡

በአድልዖ፡ በሙስና፡ በዘር ክፍፍሉ
በስጋት፡ ተስፋ እጦት-
አንገቱን ከሚሰብር ፡
አልወልድም ይቅርብኝ - ባልም አላገባ
ይበሉኝ ቆሞ ቀር፡፡